**አንዳንድ ነጥቦች ስለ አዳም ረታ እና ስለ ድርሰቶቹ**

**ቴዎድሮስ አጥላው**

መስከረም 25፣ 2007 ሐገር ፍቅር ቴአትር

"ኮስታራ ከሆነ ወይም የሰባ የስነፅሑፍ ወይም የባህል ሂስ ካለበት ህብረተሰብና፤ ልብወለዱ እንኳን ንኡስ ዘውጎች ያልተሰየሙለት (ነገር ግን ) ዘመናዊ ከተባለ የስነጽሑፍ ባህል የተመዘዝኩ ነኝ፡፡ ይሄ እጥረት በሆነ መልክ ድጋፍ ያጣሁ ደራሲ ያደርገኛል፡፡ የራሴን ፍልስፍና ስናገር በአገራችን የመፃፍ ካርታ ላይ ከማንና የትጋ እንደምታስቀምጠው ግራ ሊያጋባ ይችላል፡፡ ይሄ ባይተዋርነት ሆነ ተብሎ ከሚሰነዘር አግላይነት ጋር ሲደመር ሕፅናዊነት የሚለው ቃል ገቺ ወይም ኢጋጅነት ይኖረዋል፡፡"

አዳም ረታ፤ አብሮነት- ነፃራዕይ ቅፅ 6

አዳም በሚፈጥራቸው ታሪኮች፣ በታሪኮቹም ልብ ሰቃይ ሁነቶች ወይ ድርጊቶች፣ ወይም ያንጠለጠለውን ልብ፣ ያጦዘውን ታሪክ በማርገብ በሚያሳርፍባቸው ቴክኒኮቹ የምናደንቀው ደራሲ አይደለም፡፡ ካነበብንለት ከስልሳ በላይ ድርሰቶቹ የስንቶቹ ታሪክ ፍፃሜ አጓጓን? (ከ"መረቅ" ውጭ)

አዳም ልማድ ከራርሞ ደንብ ያደረገውን የአፃፃፍም የአነባበብም ቅጥ አፍርሶ ካንባቢ የተዋወቀ፣ ካንባቢ የተግባባ፣ ካንባቢ የተወዳጀ ደራሲ ነው፡፡ በ "ማኅሌት" የስነጽሑፎቻችንን ነባር ልሂቃን ያስደነገጠ፣ (ምናልባትም በዚህም ከመደነቅ ይልቅ መገለልን የተቀበለ)፣ ምናልባትም "ከመገለል" እና "ድጋፍ ከማጣት" ብሽቀት ራስን ወደ ማግለል ተሸጋግሮ ከቆየበት 16 ዓመት በኋላ ደግሞ በ"ግራጫ ቃጭሎች" ሲመለስ የሥራውን ርቅቀት ያህል በአንባቢም በሐያሲም ዘንድ የስነፅሑፍ ካርታ ላይ የሚያርፍበትን ሥፍራ በጊዜ ያላገኘ፣ ነገር ግን ቀስ በቀስ በኢትዮጵያ ስንፅሑፍ ካርታ ላይ የብቻነት ደሴትም ቢሆን መቆያ ሥፍራ በማግኘቱ፣ ተከትለው በመጡት አምስት የአጫጭር ልቦለድ መድብሎች አማካይነት የደሴቱን መለያ ቀለም፣ መተዳደሪያ ደንብ ቀምሮ ለአገሩ ስነፅሑፍ የሚሆንም ደንብ በማበጃጀት ላይ ያለ ደራሲ ነው፡፡

አዳም በደራሲነቱ (በደንብ ጣሽ ደራሲነቱ) ስድስት የአጫጭር ልብወለድ መድብሎችን እና የዛሬውን መረቅ ጨምሮ ሁለት ረጃጅም ልብወለዶችን ሰጥቶናል፡፡ የአማርኛ ስነፅሑፍ ዘመናዊ የሚልን ቅፅል ከፊቱ አስቀድሞ ከሚጠናበት ዘመን ጀምሮ ነባሩን ደንብ ሲጥሱ የታዩ፣ አለማየሁ ገላጋይ "በጥባጭ ደራሲዎች" ብሎ ከሚጠራቸው መሐል የሚመደቡ ሌሎች ደራሲዎች ነበሩን፤ አሉንም፡፡ በዝርው ድርሰት ዳኛቸው ወርቁን እና ስብሃት ገብረእግዚአብሔርን ብንጠቅስ፣ በግጥም ሰሎሞን ደሬሳን ዋቢ ልንጠራ እንችላለን፡፡

ለእነዚህ ደራሲዎች ስብሃትን (የቅርባችንን) ብንተወው፣ ዳኛቸው በአደፍርስ ድርሰቱ ተቀባይኘትን ከማጣት፣ እስከመተቸት፣ ከገበያም መፅሐፉን ሰብስቦ ለማሸግ እስከሚያደርስ ጉዳት ደርሶበታል፤ ሰሎሞን ደሬሳ ከጋዜጣው ላይ ነቀፋ ጀምሮ መስኮት የሚባል የግጥም እና የትችት መፅሐፍ እስኪፃፍበት ድረስ የማግለልን ገፈት ቀምሷል፡፡ እነዚህ ደንብ ጣሽ ደራሲዎች ልቦለድ እና ግጥሞቻቸውን ከመስጠት ባሻገር ቀመራቸውን የማስተዋወቅ- ኧረ የመቀመርም ጥረት አልታየባቸውም፡፡ (የሰለሞንን የ "ወሎታት" ትንታኔ አልዘነጋሁም፡፡)

አዳምን ከእነዚህ ደራሲዎች የሚለየው የሚደርስበትን ደንብ እየሠራ ያለ፣ ደንቡንም ከግራዓ ቃጭሎች ጀምሮ ለሃያሲም፣ ለደራሲም፣ ለአንባቢም፣ ለመግለጥ፣ ለማስረዳት፣ ለመግባባት በመጣር ላይ ያለ፣ ይህን ረቂቅ ነው ቢባል የማይታፈርበት የአደራረስ ደንቡን ከኖረበት ባህል፣ ካደገበት እንጀራ የቀመረ፣ እሱንም ሕፅናዊነት ብሎ የሰየመ በመሆኑ ነው፡፡ የስነፅሑፍ ቲዎሪዎች/መቅረቢያ ዘዴዎች ብዙውን ጊዜ ድርሰቶችን የስነፅሑፍ ሥራዎችን ተከትለው የሚመጡ ይመስለኛል፡፡ አዳም ጋ ግን ሁለቱንም በትይዩ እናያለን፡፡ የመድረስ ሒደቱ፣ ኅፅናዊነትን ከመቀመር ሒደቱ ጋር ጎን ለጎን የሚሠራ ይመስላል፡፡

እነ "ከአድማስ ባሻገር"፣ እነ "ሀዲስ"ን፣ እነ "ፍቅር እስከ መቃብር"ን፣ እነ "የቴዎድሮስ እንባ"ን፣ እነ "ሌቱም አይነጋልኝ"ን የምንወድበት፣ እነ "አጥቢያ"ን፣ እነ "ኗሪ አልባ ጎጆዎች"ን፣ እነ "ከጥቁር ሰማይ ስር"ን የምናደንቅበት ይሄ የአደራረስ ደንብ ምን አለውና ነው ኅፅናዊነት የሚል የአደራረስ ደንብ የሠራው? - እንጀራ ከፈጠረበት "ኢምፕሬሽን" (አዲስ መገለጥ) በተጨማሪ፣ በነባሩ የድርሰት አፃፃፍ በተለይ አንድን ሴራ እየተከተሉ (ያለ ወሽመጥ፣ ያለ ትዝታዎች) በቀጥታው መፃፍ አዳም

እንደሚለው የድርሰቱን “የመስፋፋት ድብቅ ኃይል” ማፈን ነው፡፡ የኅፅናዊነትን ጉዳይ አዳም ቀምሮ “ማኒፌስቶውን” እስኪሰጠን ለእሱው ማብራሪያውን ትቼ፣ አዳም ለዚህ አዲስ ቲዎሪ /ደንብ/ የአደራረስ ቅጥ/ ወይም የመሄሻ ዘዴ መትጋቱ በኢትዮጵያ ስነፅሑፍ ውስጥ ያመጣቸዋል ብዬ ተስፋ የማደርጋቸውን ሁለት ነጥቦች ላንሳ፡-

1 “ማንኛውም ልቦለድ አያልቅም” አዳም ረታ

“No text is complete…” Helen Reguero Elam

አዳም ቴክስቶች ከሌሎች ቴክስቶች ጋር እና አንድ ቴክስት ውስጥ ያሉ ዩኒቶች (አሐዶች) እርስ በርሳቸው የሚናበቡትን፣ እና የሚደጋገፉበትን ኢንተርቴክስቹዋሊቲ እና ኢንትራቴክስችዋሊቲ አጣምሮ በፈጠረው የኅፅናዊነት ስልቱ መነሻ የሚያደርገው በራሱ ምሉዕ የሚሆን ድርሰት የለም የሚል፣ የአውደ ንባባዊነት ዘዴ አቀንቃኞቹም የሚጋሩት ሐሳብ ነው፡፡ ይህንንም በግራጫ ቃጭሎች በቀይ ቀለም ተጠቁመው እንደ ሃይፐርሊንክ ክሊክ ቢደረግባቸው የተዛመዱበትን ዝርዝር የሚያመጡ ወሽመጦች ናቸው፡፡ መግለጫዎቻቸው ከኋላ ቀርበውላቸዋል፡፡ “እቴሜቴ ሎሚ ሽታ” ውስጥ የተጠቆሙት ኅፅኖች ሙሉ ሙሉ ታሪክ ይዘው መጥተዋል፡፡ የሎሚሽታ እና የፍቅረሥላሴ ታሪክ፣ መስኮት ገረሱን ይጠራል፣ መስኮት ገረሱ ደግሞ ስብሃትን ያስታውሳል፣ ገፀባህርይ ሆኖ የገባው ስብሃት (“ስምንተኛው ጋጋታ” የተባለ ድርሰቱ ውስጥ 'ሰው ተረት ነውና' እንዳለው፣ ተረት ሆኖ የመጣው ስብሃት)፣ የእውኑን ደራሲ ስብሃት ለአብን ከነድርሰቶቹ ያስታውሰናል፡፡ በ“መረቅ” ደግሞ ቴክኒኩ ይበልጥ ተራቅቆ መጥቷል፡፡

በነባሩ (ልማዳዊው) የስነፅሑፍ ሂስ መንገዳችን አንድ ድርሰት ወይም የስነፅሑፍ ሥራ ራሱን ችሎ የሚቆም ነው የሚል premise ይዘን ድርሰቱን በአንድ ጭብጥ፣ በአንድ ዓላማ እንገድበው ነበር፡፡ ለዚህ ደግሞ ድርሰቱ “መቋጫ ያለው፣ ውጥረቶቹን የተፈጠሩ ግራ አጋቢ ነገሮች መፍትሔ የሚያገኙበት” ነው የሚል መነሻ ስለምንይዝ - ጡዘት ቢሉ ልቀት ለሌለው፣ የወሽመጥ ታሪኮችን በውስጥም በውጭም ለሚቀጥል ድርሰት ቦታ አልነበረንም፡፡ አሁን ግን አንድ ድርሰት ብቻውን እንደማይቆም፣ የውጭም የውስጥም ዳናዎች የሚሰሙበት፣ የመስፋፋት ባህርይ ያለው መሆኑን በአዳም ድርጊትም፣ ሐሳብም አይተናል፡፡

ስለዚህ፡-

ሀ. አደራረሳችን የድርሰቱን Linear plot ብቻ የተከተለ ሳይሆን የድርሰቱን የመስፋፋት እምቅ ኃይልም የሚያታውስ እንደሚሆን፣

ለ. ሂሳዊ ንባባችንም ገና ለገና በአንድ ርዕስ ስር ለታሰረ፣ በአንድ ጥራዝም ለቀረበ፣ አንድን ድርሰት ከአንድ ነጠላ ዓላማ ወይም ትርጓሜ ጋር የማቆራኘት ልማዳችን እንደሚቀር እና ለpossiblitities of meaning open እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

2. “የተረት ጉርሻ በጉንጬ ይገኘ አልተወለድኩም” አዳም፣ “አዲስ ነገር” ጋዜጣ

አዳም በአንደኛ መደብ ተራኪ ድርሰቱን ማስተረክ የሚወድ ይመስላል፡፡ ተደጋግሞ በሚነገርለት የመተረክ፣ የመግለፅ፣ የመሳል ችሎታው የተነሳ በተለይ ከመዝገቡ ጀምሮ በዚህ መደብ ተራኪ የተተረኩትን ድርሰቶች እንደ ደራሲው ግለ ታሪክ የመቁጠር ነገር እሰማለሁ፡፡ አዳምም ለአንዳንዶቹ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ለጥያቄዎቹ የሰጠውን ምላሾች ብንተወው እንኳን በተለይ “መረቅ” መጀመሪያ አካባቢ ምን አደከማችሁ፣ የእናተ ታሪክ፣ የኔ፣ የኔም የናንተ ነው ማለት የፈለገ ይመስል እማማ እናኑን እንዲህ ያናግራቸዋል (ነው ራሳቸው ናቸው የተናገሩን?)

"የእኔ ታሪክ ምንም ብለፋ ምንም ብቀባጥር የእኔ ብቻ አይሆን፡፡ ለካ የእሱ የእኔን ይመስላል ብለህ መታዘብ አለ፡፡ ያንተ ያንተ ተሆነ፣ የእናትህ የእናትህ ተሆነ የሰብለ የሰብለ ተሆነ እንዴት እዚህ ደረስን፡፡... ጠዋት... የቆረጥኩት የአውራ ጣቴ ጥፍር ለስንት ጉንዳን ራት ይሆናል? ባላርስም አበላሁ ማለት ነው..." (ገጽ 30)

በተርታው አንባቢ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ስነጽሑፍ እንደየአቅማቸው ሲያፍታቱ፣ በእልቅናም ሲጠሩበት የኖሩም ሃያሲያን የተመሰጡበትን ድርሰት የደራሲው ግለታሪክ አድርገው የማንበብ፣ የመናገርም ድፍረት ሲላበሱም አይተናል፤ ሰምተናል፡፡ (“ከሞጆ ሌላ ደራሲ አገኘን” ተብሏል አራት ኪሎ ተወልዶ ያደገው አለማየሁ ገላጋይ፡፡)

አዳም በመስማትም ይሁን በማየት፣ ወይም በመሳተፍ የጓደኛው፣ የማያውቀው መንገደኛ፣ የማያውቃት ግን ዝናዋን የሰማላት ሴት ሳይቀር የእሱም ታሪክ እንደመሆኑ፣ ይሄ ድርሰት የኔ ታሪክ፣ ያኛው የጓደኛዬ የሚል ፍንጭ አይሰጥም፡፡ እንዲያውም ይህን ልማዳዊ አተያይ ለማክሸፍ አቅም ባለው መልኩ አዳዲስ ቴክኒኮችን (ለግለታሪክ ጥያቄ የሚከብዱ) ተጠቅሟል፡፡ "ትይዩ" የሚለው ከሁለት ተፈላላጊዎች አንፃር በትይዩ የተጻፈ ድርሰት፣ አራት አጨራረስ (ስለዚህም ቢያንስ አራት ትርጓሜ ያለው) "ዘላን"፣ ከሦስት ተራኪዎች አንፃር የተፃፈው "እቴሜቴ ሎሚ ሽታ" በአስረጂነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

የአዳምን ግለታሪክ ማወቅ ያጓጓል፤ ድርሰቱን ለመረዳት ብሎ ግለታሪኩን ለማወቅ መጓጓት ግን የአዳምን ድርሰቶች የትርጉም ፍድፋዴ (plurality) ያሳጣል፡፡ ድርሰቶቹን እንደልብ ከመተንተን፣ እንደየልምዳችን ከመረዳት ያግደናል፡፡

አዳምም ለዚህ ይመስለኛል እኔ ከናንተ የተለየሁ አይደለሁም፤ ከማኅበረሰቡ፣ ከቋንቋውና ከባህሉ ያገኘሁትን ነው መልሼ የምሰጣችሁ የሚለን፡፡ ለአዲስ ነገር ጋዜጣ በሰጠው ቃለ መጠይቅ፡-

"ስንወለድ ቋንቋ ዘዬና ፊደል ያለበት ኅብረተሰብ ውስጥ ነው የምንመጣው፡፡ ተረት የማውቀው ተረት አንብቤ ወይም ሰምቼ ነው፡፡ የተረት ጉርሻ በጉንጩ ይዤ አልተወለድኩም፡፡ ወይም እትብቴ ላይ ቋጥሬ አልወጣሁም፡፡ በተለያየ መልክ ደራሲው ራሱን እና ውጪውን ነው፡፡"

ደራሲው ድርሰቱን በከፊል ሊሆን፣ በከፊል ላይሆን ይችላል፡፡ አዳም እያንዳንዱ ድርሰቱ ውስጥ ሊኖር ይችላል፡፡ የእሱ መኖር ግን ድርሰቶቹን የአዳም ግለታሪክ አያደርጋቸውም፡፡ ድርሰቱ ለአንባቢ ከተበተነ በኋላ፣ ከአዳም ግለታሪክ ይልቅ ድርሰቱ ውስጥ የማገኘው የእኔ ታሪክ፣ ወይም የምሳተፍበት ታሪክ ነው ትኩረቴን ሊስበው የሚገባው፡፡

የአዳም ቴክኒኮች የደራሲውን የወሳኝነት/የገዳቢነት/ የጠቅላይ ተርጓሚነት ሚና የሚታገሉም ይመስላሉ፡፡ "ዘላን"ን በአራት መደምደሚያ ሲጨርስልን - የታሪኩ ጭብጥ/ ደራሲው ሊነግረን የሚፈልገው የቱን ነው በሚል ጥያቄያችን የሚቀልድበት ይመስላል፤ "ትይዩ"ን በሁለት ተፈላላጊ (በትይዩ ባሉ) ወንድና ሴት ዓይን ስለተረከልን፣ ትርጓሜያችን የሚመነጨው ከደራሲው ጋር ከምናምታታው ተራኪ ሳይሆን፣ ሁለትም አንድም ከሆኑት ተረኮች ነው፡፡

ለነገሩ እንደ አዳም ያለ ኅፅናዊነትን በመቀመር ላይ ያለ ደራሲ በድርሰቱ ላይ የበላይነት ሚና ("authority") እንዲኖረው የሚፈቅድ አይመስለኝም፡፡

ስለዚህ፡-

ሀ. በዚህ የዳበረ፣ የረቀቀ (ወይም ብልጣብልጥ) ደራሲ ብርቅ በሆነበት የመቶ ዓመት የስነፅሑፍ ታሪካችን አዲስ አፃፃፍ ያመጣልን አዳም እሱ እንደሚለው "በስነፅሑፉ ካርታ ላይ" ብቻውን እንዳይሆንም፣ ስነፅሑፋችንም የራሱን ዘውግ ማበጀት እንዲጀምርም የአዳምን ስልት ተረድተው የሚፅፉ፣ አሻሽለው የሚደርሱ ሌሎች ደራሲያን ቢነሱ "ኮረጁ" ብለን ከማግለል፣ እንደምናበረታታቸው ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ (ያልተኮረጀ ነገር የታለና! )

ለ. የአዳም መንፈስ የሚፅፉበት መንገድ ከሚፅፉት ሐሳብ/ታሪክ እኩል የሚያሳስባቸው ደራሲዎች እንደሚያፈራልንም ተስፋ አደርጋለሁ፡፡